የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ሐምሌ 22 2014
ቀን/DATE:
ቁጥር/REF NO: 0Z/247/232/14

ለሁሉም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርትና ፕሮግራሞች ቀረጻ፣ ክለሳና ማጽደቂያ መመሪያን ስለመላክ</u>፤

ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀፅ 86 ንዑስ አንቀጽ 1፣5 እና 13 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና አተገባበር ከዓለም አቀፍ እድገት፣ ከሀገራዊ ፍላጎት እና መመዘኛዎች ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን፣ ሀገራዊ ዝቅተኛ የትምህርት ብቃት መመዘኛዎችን እንደሚያዘጋጅ፣ ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሰራር ስነ ስርዓትን እንደሚያወጣ እንዲሁም የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከፍቷቸውን ፕሮግራሞች ከሀገሪቱ የልማት ፕሮግራሞች ፋይዳና አስፈላጊነት አንጻር ተጠንተው ሲቀርቡለት አግባብነታቸውን አረጋግጦ እንደሚያጸድቅ ይደነግጋል፡፡

በዚሁ መሠረት የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓት-ትምህርት ቀረፃ፣ ክለሳና ማጽደቂያ ማስፈፀሚያ መመሪያ ተዘጋጅቶና በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ መመሪያ ቁጥር 917/2014 ሆኖ የፀደቀ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ
  <u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>

# የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርት

# ቀረጻ፣ ክለሳና ማጸደቂያ መመሪያ ቁጥር 917/2014

**Higher Education Academic Programs and Curriculum Design, Review and Approval Directive No 917/2022**

**ትምህርት ሚኒስቴር**

**Ministry of Education**

## መቅድም

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአዳዲስ ትምህርት ፕሮግራሞች አከፋፈትና የሥርዓተ ትምህርት ትግበራው ከማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጦች አንጻር ተገቢነታቸውን በቀጣይነት መፈተሽና መከታተል በማስፈለጉ፤

የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትን ከሀገራዊ ስታንዳርድ ጋር በማጣጣም የትምህርትን ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞችን የመክፈትና ነባር ፕሮግራሞችን የመከለስ ሂደት በተቋማት መካከል የተናበበ አተገባበርን የሚከተል እንዲሁም አላስፈላጊ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ድግግሞሽን በማስቀረት ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎቶች ወቅቱን የጠበቀ ምላሽ ሰጪ የአሰራር ስርዓት የሚተገበርበትን የህግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የትምህርት ፕሮግራሞች እና የሥርዓተ ትምህርት አቀራረጽ ተማሪዎችን ተፈለጊውን እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት የሚያስጨብጡ ወይም ብቁ የሚያደርጉ ሆነው እንዲቀረጹ በማስፈለጉ፤

በመሆኑም የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 34 (2) እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀፅ 86 ንዑስ አንቀጽ 5 ለትምህርት ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## PREAMBLE

**WHEREAS,** it has become necessary to ensure continuous monitoring during the opening of new academic programs and curriculum implementation at Higher Education Institutions to confirm that programs remain relevant in terms of the socio-economic needs and validate changing demands of the society;

**WHEREAS,** it has become necessary to assure quality of education and relevance and alignment of the programs and designing of curricula with the national standards;

**WHEREAS,** it has become necessary to lay down appropriate legal framework to open new programs, diminish differences, avoid redundancy/duplication of programs and curricula as well as to review the programs and curricula in similar procedures to respond timely for the needs of socio-economic development of the country;

**WHEREAS,** requiring that academic programs and curriculum development approaches are intended to equip students with the required knowledge, skills and attitudes; Or to equip the students with required competence;

**NOW, THEREFORE,** based on the authority vested in the Ministry of Education, and in accordance with proclamation 1263/2014 Article 34 (2) of the definition of powers and duties of the Ministry, and of Higher Education

Proclamation No 1152/2019 with article 86 sub article 5, it is hereby declared as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ-ትምህርት ቀረጻ፣ ክለሳና ማጸደቂያ መመሪያ ቁጥር 917/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 1. Short title

This directive may be cited as the **"Directive for Higher Education Academic Programs and Curriculum Design, Review and Approval No 917/2022"**

### 2. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተጠሪ በሆኑ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርትን የመቅረጽ፣ የመከለስ እና የማጽደቅ ስራዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

### 2. Scope of Application

This directive shall apply to the formulation, revision and approval of academic programs and curricula in government Higher Education Institutions accountable to the ministry as well as private Higher Education Institutions.

### 3. ትርጓሜዎች

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 1152/2011 ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላትና አገላለጾች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"የአካዳሚክ ፕሮግራም"** ማለት ሞጁሎች ወይም ኮርሶችና ተዛማጅ ተግባራትን አካቶ የተለየ የመማር ውጤትን የሚያመላክት የተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት ያለው እና መርሀ ግብሩ ሲጠናቀቅ ዲግሪ ወይም ሰርተፊኬት የሚያሰጥ ነው።

2/ **"ኮሌጅ/ኢንስቲትዩት/ትምህርት ቤት"** ማለት በስሩ ያሉና ተመሳሳይ ግብዓትን የሚጋሩ የትምህርት ክፍሎች ሆኖ የአካዳሚክ፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን የሚያስተባብርና

### 3. Definitions

Unless the context requires, in this directive words and expressions shall have the meaning given to each word and phrase in Higher Education proclamation No1152/2019. In addition, in this directive:

1/ **"Academic Program"** shall mean a combination of modules and/or courses, related activities, as well as approved curriculum organized for the achievement of specific learning outcomes, and that its completion leads to the award of specified degree/certificate.

2/ **"College/Institute/School"** shall mean an academic unit of a Higher Education Institutions that coordinates and oversees the academic, research, and community



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የሚከታተል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ስራ ክፍል ነው።

3/ "ሥርዓት ትምህርት" ማለት ከምሩቃን የሚጠበቁ መገለጫ ባህርያትን ለማሳካት የሚረዱ የመማር ማስተማር ሂደትንና የምዘና ተግባራትን የሚያመላክት የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ዋና ሰነድ ነው።

4/ "የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ 1263/2014 አንቀጽ 60(1) የተቋቋመ የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካል ነው።

5/ "የትምህርት አሰጣጥ አግባብ" ማለት በመደበኛ፣ በተከታታይ፣ በርቀት እና በበይነ መረብ ወይም በቅይጥ ፕሮግራም ትምህርት የሚሰጥበት ዘዴ ነው።

6/ "ሴኔት" ማለት በአዋጁ በተገለጸው መሰረት የአካዳሚክና ተዛማጅ ስራዎችን የሚቆጣጠርና የሚመራ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካል ነው።

7/ "የፆታ አገላለጽ" በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያካትታል።

## 4. ዓላማዎች

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፡-

1/ የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርቶች ከዓለም አቀፍ፣ ከቀጠናዊ፣ አገራዊና አካባቢያዊ የልማት አጀንዳዎች ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ለማድረግ፤

2/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርቶች

service activities of departments within it, which share similar resources.

3/ **"Curriculum''** shall mean a main document of academic programs that encompasses all aspects of teaching-learning and assessment delivered by programs towards the attainment of learning outcomes and the acquisition of graduate attributes.

4/ **"Education and Training Authority"** shall mean an autonomous federal government body that established by proclamation 1263/2014 article 60(1).

5/ **"Modes of Delivery**" shall mean a program delivered in regular, continuing, distance learning, virtual or mixed methods.

6/ **"Senate''** shall mean the body of Higher Education Institutions, which regulates and directs the academic and related works of the Higher Education Institutions as indicated in the Proclamation.

7/ **Gender Reference:** In this Directive, all expressions using the masculine gender applies to the feminine.

## 4. Objectives

The objectives of this directive are:

**1/** To align Higher Education academic programs and curricula with international regional, national and local priority development agendas;

**2/** To ensure that Higher Education Institutions academic programs and

የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦችና ፍላጎቶችን ማርካቱን ለማረጋገጥ፤

3/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርቶች አለማቀፋዊና አገራዊ ስታንዳርዶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ፤

4/ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርቶች የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎቶች ምላሽ በሚሰጥ አግባብ ወቅቱን ጠብቀው እንዲከለሱ ለማድረግ፤

## 5. የአሰራር መርሆዎች

1/ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 18 (2) እና 20 (7) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርትን የመቅረጽ፣ የመከለስና የማጽደቅ ሂደት በሚከተሉት መርሆዎች መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል።

ሀ. ተገቢነት

ለ. ጥራት

ሐ. አሳታፊነት

መ. ነፃነት

ሠ. ተጠያቂነት

ረ. ተወዳዳሪነት

ሰ. ውጤታማነት

curricula satisfy the social and economic development of the society;

3/ To ensure that Higher Education Institutions academic programs and curricula meet the global and national standards;

4/ To review academic programs and curricula periodically to respond to the socio-economic demands of the society;

## 5. Guiding Principles

Without prejudice to principles provided in Proclamation **1152/2019** article 18 (2) and 20 (7), Higher Education Institutions shall have the following principles in designing, reviewing and approving the Higher Education academic programs and curriculums:

- **a.** Relevance
- **b.** Quality
- **c.** Participatory
- **d.** Autonomy
- **e.** Accountability
- **f.** Competitiveness
- **g.** Efficiency

# ክፍል ሁለት
# የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ቀረፃ፣ ክለሳና ማጽደቅ

## 6. የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ቀረፃ

1/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከውስጥም ሆነ ከውጭ አካላት ፍላጎት የመነጩ አዳዲስ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን ሊከፍት ይችላል።

2/ በንዑስ አንቀጽ (1) የቀረበው አዲስ ፕሮግራም የመክፈት ፍላጎት ለተቋሙ ሴኔት ቀርቦ ውይይት ይደረግበታል።

3/ በየትኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጠው የአካዳሚክ ፕሮግራም ለተቋሙ ልዩ ካልሆነ በስተቀር ከሌሎች ፕሮግራሞች ጋር መዋሃድ አለበት።

4/ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ከኮርሶች ሁለት ሶስተኛው ይዘት ተመሳሳይ ከሆነ ይዋሃዳሉ።

5/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚከፍተውን አዲስ ፕሮግራም ዘላቂነቱን ለማስጠበቅ ለደረጃው ከሚያስፈልገው የሰው ሀብት 75 በመቶ መሟላቱን የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

6/ የሚከፈተው አዲስ የአካዳሚክ ፕሮግራም ቅድሚያ ከተሰጣቸው ሀገራዊ የልማት መስኮች፣ ከዩኒቨርሲቲዎች ትኩረት መስክና ተልዕኮ ልየታ ሰነድ እና ከትምህርት ፖሊሲ ጋር የተሳሰረ ይሆናል።

7/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚከፍተውን አዲስ የአካዳሚክ ፕሮግራም በተለያዩ ሴክተሮች፣ ተማሪዎችና ማህበረሰቡ ዘንድ ፍላጎት መኖሩን የሚያረጋግጥለት የዳሰሳ ጥናት ከተቋም ውጭ ያሉ ተመራማሪዎችን በማሳተፍ ጥናቱ እንዲከናወን ያደርጋል።

# PART TWO
# ACADEMIC PROGRAM DESIGN, REVIEW AND APPROVAL

## 6. Academic Program Design

1/ Any Higher Education Institution can initiate the opening of new academic programs that can be originated from the interest of internal or external bodies.

2/ The program that is initiated in sub article (1) of this article shall be presented to the institution's Senate.

3/ An academic program offered by any Higher Education Institution shall be combined with other programs unless it is exclusive and unique to the institution.

4/ Two or more academic programs shall be merged if two-thirds of the course content is the same.

5/ In order to maintain the sustainability of any new program opened by any institution of higher education, it must provide information showing that 75 percent of the human resources required for the level have been met.

6/ The initiated program shall be in line with university differentiation framework, the national development priority and education policy.

7/ A need assessment shall be carried out by involving researchers from outside the institution to ensure that there is need in the various sectors, potential students and the community for the new academic program to be opened by the Institution of Higher Education.

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

8/ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናቱ አገር አቀፍ አካታችነቱን ጠብቆ መከናወን የሚገባው ሲሆን ሊማሩ የሚችሉ ተማሪዎች፣ ቀጣሪዎች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ የሙያ ማህበራት፣ የውጭ ገምጋሚዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች በመረጃ ሰጪነት በጥናቱ ይታቀፋሉ። እንዲሁም የሚከፈተው የአካዳሚክ ፕሮግራም ቅርጽ፣ ተገቢነትና ይዘት ዓለምአቀፍ ተሞክሮዎችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

9/ በማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነባር የአካዳሚክ ፕሮግራም ሲለወጥ በማስረጃ ላይ በተመሰረተ ሰፊ ጥናት፣ ቅድሚያ ለተሰጣቸው አገራዊ የልማት አጀንዳዎች እና ዓለማ አቀፍ ተሞክሮዎችን ማካተቱ ተረጋግጦ በሚኒስቴሩ ይመዘገባል።

8/ The needs assessment study shall be conducted at national level and should include potential students, employers, industries, professional associations, external reviewers and other relevant stakeholders to get feedback, and international experiences regarding the design, relevance and contents of the new program to be launched.

9/ When the existing academic program of any institution of higher education is changed, it will be confirmed and recorded by the Ministry through extensive evidence-based research, inclusion of prioritized national development agendas and international experiences.

## 7. የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ክለሳ

1/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጣቸውን የአካዳሚክ ፕሮግራሞች የትምህርት ፖሊሲን መሰረት አድርጎ እንደ የፕሮግራሞቹ የጊዜ እርዝማኔ ከአራት እስከ ስድስት ዓመት ባለ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወቅቱን ጠብቆ መከለስ ይኖርበታል።

2/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የአካዳሚክ ፕሮግራም ክለሳ ስራ ሲያከናውን የተዋደደውን የከፍተኛ ትምህርት ሌጅስሌሽን፣ የተልዕኮ ልየታ ሰነድ፣ አገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ብቃት ማዕቀፍ፣ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች አክርዲቴሽን ስትራቴጂ፣ አገራዊ የልማት አጀንዳዎች እና ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መነሻ ማድረግ አለበት።

3/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም

## 7. Academic Program Review

1/ The academic programs offered by any institution of higher education shall be periodically reviewed based on the educational policy within a period of four to six years depending on the duration of the programs.

2/ Any Higher Education Institution program review shall give attention and reference to the harmonized legislation, differentiation framework and strategy, Ethiopian educational qualification framework, academic program accreditation strategy, national development agenda and international experience.

3/ Any Higher Education Institution shall



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ቢያንስ ሶስት የውጭ ገምጋሚዎችን በተቋሙ መመሪያ መነሻነት በነጻ ውድድር ላይ ተመስርቶ ከዩኒቨርሲቲዎች ወይም ከምርምር ተቋማት ወይም ከኢንዱስትሪዎች በዩኒቨርሲቲው የፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርት ሴኔት ቋሚ ኮሚቴ ተለይቶና ተገምግሞ በመጋበዝ ሊከለስ የተፈለገውን የአካዳሚክ ፕሮግራም ከማስተማርና ከምርምር አኳያ በገለልተኛነት እንዲገመግሙ ማድረግ አለበት።

4/ የተጋበዙ የውጭ ገምጋሚዎች አገራዊ የግምገማ ዐውደ ጥናት ከመካሄዱ ከአንድ ወር ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ፕሮግራሙን ለመከለስ የተዘጋጀው ፕሮፖዛል እና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

5/ ሊከለስ የተፈለገው የአካዳሚክ ፕሮግራም ከመጽደቁ በፊት ዩኒቨርሲቲው በሚያዘጋጀው ተቋማዊና አገራዊ የማረጋገጫ ዐውደ ጥናቶች ከመስኩ ባለድርሻዎችና ገምጋሚዎች የሚሰጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ግብረ መልሶችን ማካተት ይኖርበታል።

6/ በየትኛውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተከለሰ ነባር የአካዳሚክ ፕሮግራም በሚኒስቴር መስሪያቤቱ እንደገና ተፈትሾ መመዝገብ ይኖርበታል፤ እንዲሁም እውቅና በሚሰጥ አካል እንደገና እውቅና እና ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት ይኖርበታል።

invite at least three relevant and well experienced senior external reviewers based on the institution's guideline with free competition by the Senate Standing Committee for Academic Standards and Program Review from different universities or research institutes, or industries. The external reviewer is required to be independent of the proposed program in terms of teaching or research affiliation to the department.

4/ The external reviewers shall get the draft academic program proposal and need assessment report documents not later than one month before conducting the national workshop.

5/ Prior to the approval of the reviewed academic program, higher education intuitions shall organize institutional and national level validation workshop and incorporate the constructive comments and feedback from stakeholders and reviewers from the workshop.

6/ Reviewed academic programs in any Higher Education Institution shall be re-registered at the Ministry and apply for accreditation and licensing to accrediting body.

## 8. የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን ስለማጽደቅ

1/ የተቋሙ ሴኔት ለመክፈት የተፈለገውን አዲስ የአካዳሚክ ፕሮግራም የማጽደቅ ወይም ያለማጽደቅ ስልጣን አለው። ሴኔቱ የሚከፈተውን ፕሮግራም ሲገመግም በስተራቴጂያዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል። ሴኔቱ ከተቋሙ ተልዕኮ እና ስትራቴጂያዊ ዕቅድ፣ ቅድሚያ ከተሰጣቸው የልማት መስኮች፣ ከሌሎች ፕሮግራሞች ልዩ የሆነበትን፣ ፕሮግራሙን ለመተግበር የሚያስፈልግ የሀብት አቅርቦት እና

## 8. Academic Program Approval

1/ The University Senate shall have the power to approve or reject the proposed new program. The Senate shall focus on strategic issues in reviewing the programs. The criteria for approval include relevance of the new program to the institution's mission and strategic plan as well as national priorities, uniqueness of the proposed program vis-à-vis existing programs, resource



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ከምሩቃን የስራ ዕድል አኳያ ፕሮግራሙ ያለውን ተገቢነት በዝርዝር መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ በመገምገም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2/ የሴኔቱ ውሳኔ በአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚደንት አማካኝነት ለሚመለከታቸው የአካዳሚክ ስራ ክፍሎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተደራሽ ይደረጋል፡፡ ለአዲሱ ፕሮግራም ተማሪዎችን መቀበል የሚቻለው ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ህጋዊ ፍቃድ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

3/ አዲሱን የአካዳሚክ ፕሮግራም ለመክፈት የተከናወነ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ግኝቶች፣ ቃለጉ ባኤዎች እና የተካሄዱ የግምገማ እና የማረጋገጫ ዐውደ ጥናቶች ሪፖርቶች በየደረጃው በጥልቀት ተመርምረው መጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

4/ የተቋሙ ቦርድ ሊከፈት የተፈለገው የአካዳሚክ ፕሮግራም ከአገሪቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅድና ከተቋሙ ተልዕኮ፣ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ስትራቴጂዎች እና ከተቋሙ ሌጅስሌሽን ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

5/ የተቋሙ ቦርድ የሚከፈተውን የአካዳሚክ ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግና ዘላቂነቱን ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆነ ሰብዓዊና ቁሳዊ እንዲሁም የፋይናንስ ሀብት በበቂ ሁኔታ መቅረቡን፤ እና ከፕሮግራም ስታንዳርዶች አንጻር ተገቢነቱን ያረጋግጣል፡፡

6/ የተቋሙ ቦርድ ከአገራዊው የትምህርት ብቃት ማዕቀፍና ከአካዳሚክ ፕሮግራሞች አክርዲቴሽን ስትራቴጂ አንጻር የትምህርት ፕሮግራሙን የጥራት መለኪያ አነስተኛ ስታንዳርዶች፣ ተፈላጊ ሀብት እና የአመራር አደረጃጀት መሟላቱን ያረጋግጣል፡፡

7/ የተቋሙ ቦርድ አዲስ በሚከፈተውና በነባር

implications to run the program, and market niche.

2/ The official decision of the Senate shall be communicated in official letter to colleges within one month through the Academic Vice President with a copy to the institution's registrar and other concerned offices. Admission of students to this new program shall take place only after the endorsement of the Ministry.

3/ The needs assessment findings, minutes and reports of the workshop for the opening of new program shall be examined thoroughly for approval at all levels.

4/ Board of the university shall check, if the new program is consistent with the country's strategic plan and with the mission, strategic priorities and legislation of the Higher Education Institutions.

5/ The Board shall ensure that there are sufficient resources (physical, human and financial) to run and sustain the academic program and the academic standards of the program are appropriate to the proposed level and title of credential awarded.

6/ The university shall ensure that the educational program's minimum standards of quality measurement, required resources and management organization are met in view of the national educational qualification framework and the accreditation strategy of academic programs.

7/ The board shall ensure that there is no duplication between the new and



Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education

የአካዳሚክ ፕሮግራሞች መካከል ድግግሞሽ አለመኖሩን፤ የአዲሱ ፕሮግራም ምሩቃን በስራ ገበያው፣ በኢንዱስትሪውና በቀጣሪዎች ተፈላጊ የሙያ ባለቤት የሚያደርጋቸውን ይዘት ማሟላቱን ያረጋግጣል።

8/ የተቋሙ ቦርድ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች መመዝገባቸውንና እውቅና ማግኘታቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል።

9/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በጽሑፍ የተገለጸ ፍቃድ ሳያገኝ አዲስ የአካዳሚክ ፕሮግራም መክፈት አይችልም።

## ክፍል ሦስት
## የሥርዓተ-ትምህርት ቀረፃ፣ ክለሳና ማጽደቅ

### 9. የሥርዓተ-ትምህርት ቀረፃ

1/ ማንኛውም አካዳሚክ ፕሮግራም አስፈላጊና ተገቢ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ይኖረዋል። በስታንዳርዱ መሰረት ተፈላጊ ሁኔታዎችን ያሟላ ሥርዓተ ትምህርት መቀረጹን ተቋሙ ያረጋግጣል።

2/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ስራው ከአገራዊው የተቋማት ተልዕኮና ትኩረት መስክ ልየታ ሰነድ፣ የብቃት ማዕቀፍና ከአክርዲቴሽን ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

3/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየመንፈቅ ዓመቱ የሚሰጡ ዝቅተኛና ከፍተኛ የኮርሶች ክብደት መጠን፣ በትምህርት የቆይታ ጊዜ ውስጥ የኮርሶች ድልድል ወይም ክፍፍል እና ፕሮግራሙን ለማጠናቀቅ መወሰድ የሚገባውን credit hours ወይም ተመጣጣኝ ECTS በአግባቡ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

existing programs within the institutions, there is market demand for the new academic program, and its learning outcomes address the requirements of students, industry, employers and professions.

8/ The Board shall monitor and ensure the registration and accreditation of the academic programs.

9/ Any Higher Education Institution shall not endorse new academic program without written permission from the Ministry.

## PART THREE
## CURRICULUM DESIGN, REVIEW AND APPROVAL

### 9. Curriculum Design

1/ Any academic program must have a curriculum that is consistent and relevant to the academic program. The Higher Education Institution has to ensure that all the elements or components of the curriculum are incorporated as per the standard.

2/ The Higher Education Institutions shall ensure that the curriculum development align with differentiation framework, Ethiopian Qualification Framework and Program Accreditation Strategy.

3/ The Higher Education Institutions shall ensure the semester minimum and maximum course load and the distribution of the courses across the duration of the program and the total minimum credit hours and its equivalent

4/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የቅድመ ምረቃ የአካዳሚክ ፕሮግራሙን በ4 ዓመት ለማጠናቀቅ ቢያንስ 136 Credit Hours/224 ECTS/፣ በ5 ዓመት ለማጠናቀቅ ቢያንስ 170 Credit hours/280/ ECTS፣ በ6 ዓመት ለማጠናቀቅ ቢያንስ 204 Credit Hours/336/ ECTS ኮርሶችን ያካተተ ሥርዓተ ትምህርት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል።

5/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቀረጸው ሥርዓተ ትምህርት ኮርሶች ይዘት ተገቢነትን የሚገመግም ተቋማዊ እና አገራዊ ዐውደ ጥናት ቁልፍ ባለድርሻዎችን ባሳተፈ ሁኔታ ያካሂዳሉ።

6/ በየትኛውም ነባር አካዳሚክ ፕሮግራም ላይ አዳዲስ ኮርሶችን ለመጨመርም ሆነ ነባር ኮርሶችን ለማስወጣት ፕሮግራሙን ከሚሰጡ አቻ ተቋማት ጋር ስምምነት ላይ መድረስ ይገባል።

7/ የአካዳሚክ ፕሮግራሙ ለተቋሙ ልዩና ብቸኛ ካልሆነ በስተቀር ፕሮግራሙን ከሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ ሥርዓተ ትምህርት እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

## 10. የሥርዓተ-ትምህርት ክለሳ

1/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ሥርዓተ ትምህርት የአተገባበር ደረጃውን በመረጃ ላይ ተመስርተው የፍላጎት ዳሰሳና የሁኔታ ትንተና በማካሄድ ይገመግማሉ።

2/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ፕሮግራሞችን በሚከልሱበት ወቅት የውስጥ ገምጋሚ ሆነው የሚያገለግሉ በመስኩ የተሻለ ልምድ ያላቸው መምህራን እና የትምህርት ባለሙያዎችን ማሟላት ይኖርባቸዋል።

ECTS required to complete the program.

4/ Any institution of higher education shall make sure that a curriculum that includes at least 136 Credit Hours/224 ECTS/ to complete the undergraduate academic program in 4 years, at least 170 Credit Hours/280/ ECTS to complete in 5 years, and at least 204 Credit Hours/336/ ECTS to complete in 6 years.

5/ Higher Education Institutions shall conduct in-house and national validation workshop on the relevance of the courses and its contents for the curriculum by engaging key stakeholders.

6/ Adding new courses or removing existing courses and its contents shall be rationalized and discussed with other universities running similar academic programs to reach at common agreement.

7/ Unless the program is unique to a particular institution, all curricula shall be developed together with those institutions running similar program.

## 10. Curriculum Review

1/ Higher Education Institutions shall conduct need assessment and situation analysis combined with evidence-based observations to assess the actual status of implementation of the curriculum.

2/ Higher Education Institutions shall require senior and experienced staff related to the program, and an educational specialist is to be internal reviewers. The profession of the senior

3/ በአካዳሚክ ፕሮግራም ክለሳ ስራ ላይ የሚሳተፉ የውስጥ ገምጋሚዎች ለመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች የፒ.ኤች.ዲ ምሩቅ ሆነው ረዳት ፕሮፌሰር የአካዳሚክ ማዕረግ ያላቸው፣ለሁለተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች የፒ.ኤች.ዲ ምሩቅ ሆነው ተባባሪ ፕሮፌሰር የአካዳሚክ ማዕረግ ያላቸው እንዲሁም ለሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች የፒ.ኤች.ዲ ምሩቅ ሆነው ሙሉ ፕሮፌሰር የአካዳሚክ ማዕረግ ያላቸው መሆናቸውን ተቋማቱ ያረጋግጣሉ።

4/ ተቋሙ ሊከለስ ለተፈለገው የአካዳሚክ ፕሮግራም ሦስት የውጭ ገምጋሚዎችን ከአቻ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወይም ከምርምር ተቋማት ወይም ከኢንዱስትሪው ገለልተኛ ባለሙያዎችን በመሰየም ሙያዊ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ያደርጋል።

5/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊከለስ የተፈለገውን ፕሮግራም ሥርዓተ ትምህርትና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት አገራዊ የግምገማ ዐውደ ጥናት ከመካሄዱ ከአንድ ወር በፊት ለውጫዊ ገምጋሚዎች እንዲደርሳቸው ያደርጋሉ።

6/ የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ ስራው መከናወን ያለበት ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተልዕኮ ልየታ ማዕቀፍ፣ ከአክርዲቴሽን ስትራቴጂ እና ከብቃት ማዕቀፍ አንጻር ተቃኝቶ መሆን አለበት።

7/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ስለሚካሄድበት፣ የውስጥና የውጭ ገምጋሚዎች ስለሚመረጡበት፣ ተቋማዊና አገራዊ የሥርዓተ ትምህርት መገምገሚያ እና ማረጋገጫ ዐውደ ጥናቶች ስለሚከናወኑበት ዝርዝር ተቋማዊ የአፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጃሉ።

## 11. ሥርዓተ-ትምህርትን ማጽደቅ

1/ ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም

staff must be related to the curriculum area.

3/ Higher Education Institution shall ensure that the internal reviewers must hold PhD with the rank of Assistant Professor to review the first-degree curricula, PhD with rank of Associate Professor to review second degree curricula and PhD with rank of Professor to review third degree curricula.

4/ The institution appoints three external evaluators from peer higher education institutions or research institutions or independent experts from the industry to give their professional opinion for the academic program to be revised.

5/ The Higher Education Institutions shall send the draft curriculum and the need assessment report documents to reviewers no later than one month prior to conducting the national workshop.

6/ Curriculum review shall be conducted in accordance with Ethiopian universities differentiation framework, Ethiopian Qualification Framework and Program Accreditation Strategy.

7/ The Higher Education Institutions shall issue guideline on how to conduct need assessment, recruitment/nomination of internal and external reviewers and conducting of in-house and national validation workshop, based on the minimum requirements indicated in this directive.

## 11. Curriculum Approval

1/ Any Higher Education Institution shall

ለሚከፍተው የአካዳሚክ ፕሮግራም የተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት ከዓለም አቀፋዊ፣ ከቀጠናዊ፣ ከአገራዊና ከአካባቢያዊ ፍላጎቶች አንጻር ተገቢ መሆኑን ያረጋግጣል።

2/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መርሃ ሥርዓተ ትምህርት ስለመዘጋጀቱ፣ የምዘና ዘዴዎች እና የኮርስ ይዘቶች ሽፋን ሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በተገለጸው አግባብ መካተቱን ማረጋገጥ ያለባቸው ሲሆን የትኛውም ዓይነት ልዩነት ከተፈጠረ ሥርዓተ ትምህርቱ ሊጸድቅ አይችልም።

3/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተግባር ትምህርትና ለቤተ-ሙከራ ስራዎች አስፈላጊ የትምህርት ግብዓቶችና ፋሲሊቲዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

4/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርት በትኩረት መስክ እና ተልዕኮ ልየታቸው መሰረት ከየተቋማቱ ራዕይ ጋር መዛመዱን ያረጋግጣሉ።

5/ በሚዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት ላይ የዳሰሳ ጥናት ውጤትን በማካተት የግምገማ መድረኮች በአግባቡ መካሄዳቸውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ያረጋግጣሉ።

6/ አስፈላጊ የሆኑ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ ቃለ-ጉባኤዎች እና የዐውደ ጥናቶች ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው አካላት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው።

7/ የዲግሪ ስያሜዎች ስታንዳርዱን ጠብቀው በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ እንደሚከተለው መጻፍ አለባቸው፡-

ሀ) ለመጀመሪያ ዲግሪ፡-

'የባችለር ሳይንስ/አርት ዲግሪ በ-------'

ensure that the curriculum prepared for the academic program opened by any higher education institution is appropriate in terms of global, regional, national and local needs.

2/ The Higher Education Institutions shall ensure that syllabi prepared, teaching-learning process, the assessment methods and the course contents coverage are as stated in the curriculum. Any deviation from what is stated in the curricula is not accepted and such programs are not approved.

3/ The Higher Education Institutions shall ensure that the necessary resources and facilities required for practical courses and lab works are in place.

4/ Higher Education Institutions shall ensure that the program is related to the focus area and mission of the particular institution as per the differentiation made.

5/ The Higher Education Institutions shall ensure that evaluation forums are conducted properly by including the results of the need assessment on the curriculum being prepared.

6/ All the necessary documents including the needs assessment, all minutes and validation workshop reports are to be presented to the concerned bodies for approva.

7/ The degree nomenclature by the Higher Education Institutions shall be written both in English and Amharic. It shall also be written in a standard manner.

a. For first degree:

"Bachelor of Science/Arts/ Degree in ---'



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ለ) ለሁለተኛ ዲግሪ፡-

'የማስተርስ ሳይንስ/አርት/ዲግሪ በ-------'

ሐ) ለሦስተኛ ዲግሪ፡-

'የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ በ------'

b. For second degree:

"Master of Science/Arts/Degree in--'

c. For third degree:

"Doctor of Philosophy in ...'

## ክፍል አራት
## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 12. የትምህርት ሚኒስቴር

1/ እንደ አገር ቅድሚያ ከተሰጣቸው የልማት ዘርፎች፣ ከማህበረሰቡ ፍላጎት እና ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች አኳያ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ሊያሟሉ የሚገባቸውን መስፈርቶችና ስታንዳርዶች ቅደም ተከተል ያስቀምጣል።

2/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከናወን የአካዳሚክ ፕሮግራም ዝግጅትና ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መሆኑንና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት አተገባበርና ግኝቶች በሚፈለገው ልክ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ፍቃድ ይሰጣል፤ ፕሮግራሙ እንዲመዘገብ ያደርጋል።

3/ አላስፈላጊ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ድግግሞሽን በሚያስቀር አግባብ የመንግስት ፖሊሲ መተግበሩን የመከታተልና አዳዲስ የትምህርት መስኮች ስለሚከፈቱበት አቅጣጫ ያስቀምጣል።

## PART FOUR
## ROLES AND RESPONSIBILITIES OF STAKEHOLDERS

### 12. Ministry of Education

1/ Shall establish the order of requirements and standards that academic programs must meet according to the country's priority development sectors, community needs and international experiences.

2/ Shall give permission and register program preparations and delivery of curricula of Higher Education Institutions that are in accordance with set standards, confirm the finding of the need assessment as it was conducted as per the requirement of the entire academic program.

3/ Shall monitor the implementation of government policy in a way that avoids duplication of unnecessary academic programs and sets the direction for the opening of new fields of education.

4/ Shall provide professional assistance to



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

4/ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጣዊ ጥራትን የማሻሻልና የማስጠበቅ የአሰራር ሥርዓትን ለማጠናከር ሙያዊ እገዛ ያደርጋል፡፡

5/ የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ሂደት ለአዳዲስ ግኝቶች አስፈላጊውን ትኩረት በሚሰጥ አግባብ ከተልዕኮና ትኩረት መስክ ልየታ ማዕቀፍ፣ ከብቃት ማዕቀፍ እና ከፕሮግራሞች አክሬዲቴሽን ስትራቴጂዎች አኳያ መከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

6/ በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የጋራ ኮርሶች መካተታቸውን ያረጋግጣል፤ አተገባበሩንም ይከታተላል፡፡

7/ ከፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጋር የተያያዘ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

8/ ሁሉንም የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ምዝገባ ያካሂዳል፡፡

9/ ለተመዘገቡና ለጸደቁ ፕሮግራሞች አገራዊ የመረጃ ቋት ያደራጃል፤

10/ በፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርቶች ዙሪያ ጥናት በማካሄድ አስፈላጊውን የማሻሻያ ስራዎችን ያከናውናል፤ የክትትል፣ ድጋፍ እና የቁጥጥር ስራ ይሰራል፡፡

## 13. የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን

1/ በስታንዳርድ ላይ የተመሰረተ ምዘና በማካሄድ ለአካዳሚክ ፕሮግራሞች እውቅናና ፍቃድ በመስፈርቱ መሰረት ይሰጣል፡፡

2/ በአገራዊው የአክሬዲቴሽን ቦርድ ሲጸድቅ እውቅና ለተሰጣቸው ፕሮግራሞች የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፤ የእውቅናና የዳግም

strengthen the system of improving and maintaining internal quality in higher education institutions.

5/ Shall ensure curriculum development process is conducted in accordance with differentiation framework, Ethiopian Qualification Framework and Program Accreditation strategy with due emphasis given to new findings.

6/ Shall check the inclusion of all the common courses and follow up its implementation.

7/ Works on capacity building activities in relation to program and curriculum development.

8/ Shall register all academic programs at national level.

9/ Shall organize national data base of all the registered and approved programs.

10/ Shall conduct study on programs and curricula and carries out the necessary improvement works; perform monitoring, support and supervision.

## 13. Education and Training Authority

1/ Shall provide academic program accreditation and license based on criterion and the finding of the academic program assessment;

2/ When approved by the National Accreditation Board, it shall issue certificates to accredited programs, distributes them to those concerned, and publishes and makes accessible the results of accreditation and re-



Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

እውቅና ውጤቶችን በማሳተም ተደራሽ ያደርጋል።

accreditation;.

14. ቦርድ

1/ አዲሱ የአካዳሚክ ፕሮግራም ከዓለም አቀፍ፣ ቀጠናዊ እና አገራዊ ስታንዳርዶች እንዲሁም ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልየታ ጋር መጣጣሙን ቦርዱ ያረጋግጣል።

2/ አዲሱ ፕሮግራም ከመተግበሩ በፊት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ እንዲጸድቅ ያደርጋል።

**14. Board**

1/ Board shall check, if the new program is consistent with international, regional, and national standards and the country's strategic priorities and differentiation of the Higher Education Institutions.

2/ Before the impolementation of the program, the board shall approve and endorse the newly developed academic program confirming the fullmfilement of preconditions.

15. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

1/ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች እና ሥርዓተ ትምህርቶች ዓለም አቀፋዊ ስታንዳርዶችን፣ ቀጠናዊ፣ አገራዊ እና አከባቢያዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

2/ አስፈላጊ ቃለጉባኤዎችንና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ሰነዶችን በማካተት የፕሮግራሞች ምዝገባና ማጽደቅ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ።

3/ አዲስ ፕሮግራም ለመክፈት የሚያስችሉ የትምህርት ፋሲሊቲዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣሉ፤

4/ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርቶች ወቅቱን ጠብቀው እንዲከለሱ ያደርጋሉ።

5/ ፕሮግራሞችንና ሥርዓተ ትምህርቶችን በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት በአግባቡ ይፈጽማሉ።

**15. Higher Education Institutions**

1/ Shall ensure that academic programs and curricula are based on international standards, regional, national and local needs.

2/ Shall request for permission, registration and approval of programs with all the necessary minutes and need assessment study documents;

3/ Shall confirm all the required facilities are in place to open programs.

4/ Shall ensure that periodic review of programs and curricula is undertaken;

5/ Shall implementat the programs and curricula in accordance with set standards.

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

# ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 16. የፕሮግራምና ሥርዓተ-ትምህርት የክለሳ ጊዜ

1/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ-ትምህርት ቅድሚያ ከተሰጣቸው ሀገራዊ የልማት መስኮች እና ከአለማቀፍ አዝማሚያዎች አንጻር ፕሮግራሞቻቸውን ለማስተካከል ያመች ዘንድ በየባቹ መከለስ አለባቸው፤

2/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርት ክለሳ ሪፖርቶችን ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ መላክ አለባቸው።

3/ የተከለሰው የአካዳሚክ ፕሮግራም በሚኒስቴር መስርያቤቱ እንደገና ማስመዝገብ አለባቸው፤

4/ የተከለሰው የአካዳሚክ ፕሮግራም ዳግም እውቅናና ፍቃድ በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ይሰጠዋል።

### 17. የአካዳሚክ ፕሮግራምን ስለመዝጋት

1/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን ሲዘጉ ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ ማሳወቅ እና ለህዝብ ይፋ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን

2/ ፕሮግራሙን ለመዝጋት፡-

ሀ) አሳማኝ ምክንያት ተለይቶ መቅረብ አለበት፤

ለ) ለተማሪዎችና ለምሩቃን የሚኖረውን ፋይዳ እና አሉታዊ ተፅዕኖ ቢያጋጥም ለመቋቋም የሚቻልበት ስልት መቀመጥ አለበት፤

ሐ) ተፅኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ አካላትን ቀድሞ በመለየት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፤

መ)የአካዳሚክ ሰራተኞች ምደባ ስለሚያገኙበት እና የትምህርት ግብዓት እንደገና ጥቅም ላይ ስለሚውሉበት ዕቅድ መዘጋጀት አለበት።

# PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 16. Periodic Academic Programs and Curriculum Review

1/ Any Higher Education Institutions shall review its academic programs and curriculum on completion of one batch and adjust the academic program and curriculum with country development priority and international trends;

2/ The Higher Education Institution shall submit reports of academic programs and curriculum review to the ministry;

3/ The revised academic program shall be re-registered by the Ministry;

4/ The revised academic program shall be re-accredited and licensed at Education and Training Authority.

### 17. Termination of Academic Program

1/ In any Higher Education Institutions terminating existing academic program shall be communicated to the ministry and the public as well.

2/ The proposal for terminating academic program shall include:

a) Rationalize for terminating the academic program;

b) Describe the impact of terminating the academic program on students and academic staff and identify how any negative effects will be mitigated;

c) Acknowledgement of other bodies whose programs affected by termination of the academic program have been notified;

d) Redeployment plan, describing how

existing resources will be reallocated and how academic staff reassigned.

**18. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተልዕኮ ልየታ ስርዓትን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን ከተቋማት ተልዕኮ ጋር ተሳስሮ የማይካሄድ የአካዳሚክ ፕሮግራም ተቀባይነት የለውም።

**18. Transitory Provisions**

On the approval of this directive Higher Education Institutions shall focus on their differentiation area to excel. Any academic program that is not in line with the differentiation will not be accepted.

**19. የውስጥ ህጎች እና ደንቦች**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይህንን መመሪያ ለመተግበር የሚያግዙ ተቋማዊ ስታንዳርዶችን ወይም መመሪያዎችን ሊያዘጋጁና ሊተገብሩ ይችላሉ።

**19. Internal Rules and Regulations**

Higher Education Institutions shall develop their own guidelines/directives/standards so as to help the implementation of this directive.

**20. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎችና ልማዳዊ አሰራሮች ተፈጻሚነት የላቸውም።

**20. Inapplicable Laws**

No directive or customary practice may, in so far as it is inconsistent with the provisions of this directive, be applicable with respect to matters covered under this directive.

**21. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ትምህርት ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

**21. Amendment**

This directive may be amended only by the Ministry of Education, as needed.

**22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**22. Effective Date**

This directive shall be effective from August 8, 2022 G.C

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
የትምህርት ሚኒስትር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

Professor Birhanu Nega
Minister, Ministry of Education

Berhanu Nega (Prof.)
Minister

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education